ታህሳስ **26** ቀን **2014** ዓ/ም

ለእነ ፍፁም ተ/ማሪያም

አድራሻ፥-አ/አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ **7**

ከአቶ ታከለ ሂካ ዲብል

አድራሻ፥- አ/አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ **05**

ጉዳዩ፥- <u>የቤት ኪራይ ክፍያን እንድከፍል በቀን **2/04.2014** ዓ/ም የተጻፈልኝ አስመልክቶ በተከራይ በኩል የተሰጠ ምላሽ</u>

*ታህሳስ* 22 *ቀን* 2014 *ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ከጥር* 1 *ቀን ጀምሮ በውላችን መሰረት የስድስት ወር የቤት ኪራይ ብር* 869,400 (*ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሽህ አራት መቶ*) *ብር የቤት ኪራይ እና ባለፈው ገቢ ሲደረግ የጎደለ ብር* 28,350(*ሃያ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ አምሳ*)*ብር በድምሩ* 897,750 (*ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ሽህ ሰባት መቶ አምሳ*) *ገቢ እንዳደርግ አስታውቀውኛል፡፡*

*እኔ ተከራይ ከእስዎ ጋር መጋቢት* 16 *ቀን* 2013 *ዓ/ም ባደረኩት የቤት ኪራይ ውል ስምምነት ቤትዎን ለካፌ እና ለሬስቶራንት አገልግሎት ለመጠቀም ከሐምሌ* 1 *ቀን* 2013 *ዓ/ም ለ*6(*ስድስት*) *ዓመት መከራየቴ ይታወቃል፡፡ ሆኖም እኔ/ተከራይ በስምምነታችን መሰረት የቀጣይ ወራት የቤት ኪራይ ለመክፈል ዝግጁ ስሆን፣ በተመሳሳ በእርስዎ/ አከራይ በኩል በውላችን መሠረት መሟለት የሚገባቸው፥-*

1 *ኛ*)*የኪራይ ውሉን የተዋዋልነው ከሐምሌ* 1 *ቀን* 2013 *ዓ/ም ጀምሮ ቢሆንም ቤቱ ተሰርቶ ባለመጠናቀቁ የተነሳ በውላችን መሰረት ስራዉን በጊዜው መጀመር አልቻልኩም፡፡እንዲህም ሆኖ የቤቱ በወቅቱ ሊያስረክቡኝ ባለመቻሉ፣በይበልጥ ከሚዘገይ በሚል እስዎ ጋር በመነጋገር የፍኒሽግ ስራ ያልተጠናቀቁ በሮች ጨመር በራሴ ወጭ ገጥሜ ቤቱን አሳምሬ ዝግጁ ባመድረግ ስራ የጀመርኩኝ መስከረም ወር* 2014 *ዓ/ም መጨረሻ ላይ በመሆኑን፣ ውሉን ስንዋዋል ከወሰዱት የቤት ኪራይ ቅድመ ክፍያ ውስጥ ያልሰራሁባቸው ዎራቶች የኪራ ሂሳብ ታስቦ የወደ ፊት ኪራይ ሂሳብ ውስጥ ታሳቢ እንዲደረጉልኝ፣*

2 *ኛ*) *የአራት ወር ቅድመ ክፍያ ቫትን ጨምሮ* 652,050( *ስድስት መቶ አምሳ ሁለት ሺህ አምሳ*) *ብር የተከፈልዎት ቢሆንም በውላችን አንቀጽ* 5(5.5) *መሰረት ለሚሰበሰበው ክፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ እንዲሰጡኝ በሳስብዎትም ቫትን ጨምሮ ለተከፈለ ክፍያ ምንም ሕጋዊ ደረሰኝ እስካሁን ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡ እኔም በበኩሌ የሀገር ውስጥ ገቢ ግበር የመክፈል ሀገራዊ ግዴታ ያለብኝ በመሆኑ የወጣሁትን ወጪ ሂሳቡ በማስያዝ ግብር መክፈል እንድችል የከፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ እንዲሰጠኝ፣*

3 *ኛ*) *በውላችን አንቀጽ* 5(5.2) *መሰረት አከራይ ከሚመለከተው መስራቤት ጋር በመነጋገር መብራት፣ውሃ እንደሚያስገባ ቢደነግግም የተከራየሁት ለድርጅት አገልግሎት እንደመሆቡ መጠን* 3 *ፌዝ ቆጣሪ በለማስገባትዎ የተነሳ የገባው አነስተኛ ቆጣሪ በመሆኑ በርገር፣ፒዛ እና የመሳሰሉትን በመጋገር ለተጠቀሚው በማቅረብ ባለመቻሌ ለከፍተኛ ውጭ እና ኪሳራ የዳረገኝ በመሆኑ ቆጣሪው እነዲስተካከልልኝ፣*

4 *ኛ*) *በኪራይ ውላችን አንቀጽ* 5(5.1)*አንዱ የአካራይ ግዴታ* "*አከራይ ያከራየውን ቤት በመረካከቢያ ቅጽ ለተከራይ ያስረክባል*" *ሲል የሚድግግ ሲሆን በዚህ መሰረትም እርክክብ አደርገን ስራ እንድጀምር ብጠይቅዎትም እስካሁን ፈቃደኛ ባለመሆንዎ በአንዲጉ ስራ ከሚዘገይብኝ በሚል ስራ የጀመርኩኝ ሰሆን ለወደፊት የአሰራራችን እንዲመቸን በውላችን መሰረት እርክክብ እንድናደርግ አሳስባለሁኝ፣ ከላይ በተ.ቁ* 1-4 *የተጠቀሱት በአካራይ በኩል የተስተዋሉ ውስንነቶች/ችግሮች በ*3 *ቀን ተስተካክለው ስራየን በአግባቡ እንድሰራ እንዲያደረጉ እየጠየኩኝ፣በውላችን አንቀጽ* 9(9.1) *በሚደነግገው መሰረት በመገናኘት አለመግባበቶችን በውይይት እንድንፈታ ጭምር አሳስባለሁ፡፡*

*ከሠላምታ ጋር*

ታከለ ሂካ ዲብል